መልዕክት ለተቆርቋሪዎች

አንተ ተቆርቋሪ ሰው፡

- ታገስ፣ ትዕግስትህም በአላህ ላይ ብቻ ይሁን።
- አላህ አድለቢሶችን በክብር እንደተቀበለ እወቅ።
- ጭንቀቶችን እና ትካዜዎችን በጥንካሬ እና በድፍረት ደመና ወርውራቸው።
- ምንም ዓይነት ችግር ቢመጣብህ ታገስ።
- መንገዶቹ ከፊትለፊትህ የቱንም ያህል ጨለማ ቢሆኑ ታገስ።
- ከችግር ጋር ምቾት እንዳለ፣ ከጭንቀትም ጋር እፎይታ አለ።

አንተ ተቆርቋሪ ሰው፡

- አንተን የሚያሳስብ ነገር ቢደርስብህ…
- ጥፋቶች ቢወድቁብህ…
- በጠና ብትታመም...
- ሰዎች ቢጨቁኑህ…
- በንግድ ሥራ ኪሳራ ቢያጋጥምህ…

አትናደድ፤ አትደንግጥ፣ ቤተሰብህንም አታስቀጣ፣ ለማንም አታማርር፣ በአባትህ፣ በልጅህ፣ በወንድምህ ወይም በመኪናህ ላይ የመከራውን ከብደት አታብዛባቸው። ነገር ግን አልሐምዱሊላህ (ምሥጋና ለአላህ ይሁን) በል።

- እንዲያውም፡ “አላህ ወሰነ፣ የሚሻውንም አደረገ” በል
- ለአላህ ውሳኔ እጅ ስጥ፣ እንጂ አትቆጣ!
- እንዲህ ባደርግ ኖሮ እኮ እንዲህ ይሆን ነበር አትበል፣ ይልቁንስ “አላህ ወሰነ፣ የሚሻውንም አደረገ” በል!

አንተ ተቆርቋሪ ሰው፡

- የምትፈልገውን ሁሉ የምታሳካበትን መንገድ አሳይሃለሁ!
- ነገር ግን ልቶገባበት ካሰብክ ነው።
- አንተ ጋ ያለውን እንዲቀበልህ፣ ራስህን ሙሉ በሙሉ አዘጋጅተህ ወደ እሱ መቅረብ ያለበትን ቅድመ ሁኔታ ሁሉ ማሟላት አለብህ።
- የምትፈልገውን ለማግኘት ሙሉ በሙሉ እምነትህን እሱ ጋር በማድረግ፣ መልዕክትህን በቀጥታ ወደ እሱ ላክ!
- ማን ነው ያንተን መልዕክት ለማድረስ አማላጅ የሚሆነው?
- እርሱ የንጉሦች ንጉሥ ነው፤ የአገልጋዮች ጌታ ነው፤ የመኳንንቶችም አምላክ ነው!
- እሱም በካፍና በኑን መካከል የሚያዝ የሆነው አላህ (ሱ.ወ) ነው "ነገሩም አንዳችን በሻ ጊዜ ኹን ማለት ነው። ወዲያው ይኾናልም። [ያሲን፡ 82]"
- ስለዚህ ከመግባትህ በፊት በሚገባ ተዘጋጅ
- በሌሊቱ ድቅድቅ ጨለማም ብቻህን ግባ
- በዛን ጊዜ እሱን የተቆራኙ ሁሉ በሚተኙበት ጊዜ አንተ ንቃ
- ነገር ግን ዓይኑ የማያንቀላፋው፣ ህያው የሆነው፣ ዘላለማዊው አላህ አልተኛም
- ለባሪያዎቹም እንዲህ ይላቸዋል…
- "እመልስለት ዘንድ የሚለምነኝ አለን?… ይቅር እለው ዘንድ ይቅርታ የሚጠይቅ አለን?"
- በዚህ ጊዜ ያለህን ሁሉ ለጌታህ አቅርብ… ለምነው፣ ተጣራ…
- ከዚያም ለእርሱ ልመናህን ከጨረስክ ከሦስት ነገሮች አንዱን ታሸንፋለህ።

  [1] ወይ ጥያቄህ ይሟላል…

[2] ወይም በትንሳኤ ቀን በጣም የተሻለ ነገር ያከማቾልሃል፤ በዚችም ዓለም ከምትፈልገው ብዙ አድርጎ ያስቀምጥልሃል…

[3] ወይም፣ በዚህ ልመና፣ አላህ ከወንጀሎችህ እና ከጥፋቶችህ ይጠብቅሃል፡፡

አንተ ተቀርቋሪ ሰው፡

- ልብህ በጭንቀት ከተሞላ እና ሁኔታህ ከባድ ከሆነ…
- ቀንህ ከጨለመብህ ሰላትህን አደራ!
- ሰላት ሰዎችን ከበሽታ የሚፈውስ እና ከጭንቀትና ከህመም የሚገላገል ሆስፒታል ነው፡ መልዕክተኛው በታላላቅ ተልዕኮ ወቅት ቀልባቸውን (ነፍሳቸውን) በሰላት ያስታግሱ ነበር፡ ታላላቅ ሰዎችም በመከራ በተከበቡ ጊዜ፡ ወደ ሰላትም ይጣደፉ ነበር፤ አላህም ይረዳቸዋል፤ እፎይታም ይሆንላቸዋል፡፡

አንተ ተቀርቋሪ ሆይ፡

- የተደበቀ ደግነትን አብስሬሃለሁ፣ ብሩህ ተስፋን አብስሬሃለሁ፣ የወደፊት ብሩህ ተስፋህን የነገርኩህም፡ ጥርጣሬህን በእርግጠኝነት የምትፈውስበት ጊዜ ስለሆነ ነው፡፡
- በእውነተኛ ጎህ የጨለማው ደመና ከአንተ የሚገፈፍበት ጊዜ ደርሷል፡፡
- የሐዘንህን ምሬት በጣፋጭ እርካታ የምታጥብበት ጊዜ ደርሷል፡፡
- የምስራች ተቀርቋሪው ሆይ…ማለዳው በብርሃን ይሞላልሃል!፡፡

አንተ ተቀርቋሪ ሰው፡

- ለአገልጋዮቹ ቸር ከሆነ እና ለፍጡራኑ መሐሪ ከሆነው አላህ (ሱ.ወ) ጋር እየተገናኘህ እንደሆነ እርግጠኛ ሁን፡፡

አንተ ተቀርቋሪ ሰው፡

- ጥሩ ነገር እንደሚጠብቅህ፣ ውጤቱም የተመቻቸ እንደሚሆን፣ መጨረሻውም ስኬታማ እንደሚሆን እርግጠኛ ሁን።

♦♦♦○♦♦♦

አሸናፊ ሆነ... ሃብቱንም አገኘ

ሃዋርድ ካርተር የተሰኘው የአርኪዮሎጂ እና የታሪክ ባለሙያ በግብጽ ምድር የተቀበረውን "የቱታንካሙን ሀብትን" ለመፈለግ በርካታ ጥናቶችን አካሂዷል። ሂደቱ በጣም ከባድ ቢሆንም፣ በርካታ ግምገማዎችን ያካሄደ ቢሆንም በመጨረሻ የተከበረው መዓድን የሚገኝበትን ቦታ አገኘው። ነገር ግን መዓድኑን ለማውጣት ብዙ ገንዘብ የሚጠይቅ ሆነበት፣ ሃዋርድም የሚፈልገውን ለማግኘት አንድ ባለሃብት ፕሮጀክቱን እንዲደግፍለት እና እንዲረዳው አሳመነው። እናም ያ ባለሃብት ከቁፋሮው ሂደት ጋር የተያያዙ ወጪዎችን ሁሉ ሸፈነለት።

ሃዋርድ እና የሥራ ቡድኑ በተፈለገው ቦታ ላይ አካፋ እና ዶማቸውን በመያዝ ቁፋሯቸውን ጀመሩ እና ከቀኖች ቁፋሮ በኋላ የተሳሳተ ቦታ ላይ መሆናቸውን አወቁ። ሃዋርድ ወደ ድንኳኑ በመግባት እንደገና ሌላ ስሌትን እና ልኬት መቀመሩን ተያያዘው፣ በመጨረሻም ይህ ትክክለኛ መሆን አለበት በማለት፣ ስህተቱ የት እንደነበር ለቡድኑ በማብራራት በአዲሱ ቀመር መሠረት እንዲቆፍሩ ተስማሙ። በዚህም መሠረት ሠራተኞቹ ወደ አዲሱ ቦታ ሄደው መቆፈር ጀመሩ ከጥቂት ቀኖች በኋላ ግን አሁንም በተሳሳተ ቦታ እየቆፈሩ እንደሆነ አወቁ።

የፕሮጀክቱ የገንዘብ ድጋፍ ሰጪ (ፋይናንሰር)፣ ሃዋርድ በምርምሩ እና በቁፋሮው ዘርፍ ያለውን ብቃትና ልምድ መጠራጠር ጀመረ፤ ጊዜውንና ገንዘቡን በማይጠቅም ሥራ ያባከነ ሆኖም ተሰማው፤ በዚህ ባድማ ሸለቆ ውስጥ ገንዘቡን እና ጉልበቱን አልባሌ ቦታ ላይ እንዳፈሰሰ አሰበ። ሃዋርድም ፋይናንሰሩን ትዕግሥት እንዲያደርግ እና ወጤቱን እንዲመለከት፣ ብሎም ከተሳካላቸው ብዙ

እንደሚያተርፍ በማስረዳት አንድ ዕድል እንዲሰጠው ይጠይቃል። ፋይናንሰሩም እሺ አንድ ሌላ ዕድል እሰጥሃለሁ፣ ሥራህን ያለ ምንም ሃሳብ ቀጥል በማለት ይሁንታውን ሰጠው።

ሃዋርድ ስሌቱንና ልኬቱን ደጋግሞ በመግለጽ እነዚህ ቦታዎች ውድ የሆነው መዓድን የሚገኝባቸው ቦታዎች ናቸው በማለት፣ ድጋሚ በተለዩት በእነዚህ ቦታዎች ሁሉ መቆፈር ጀመረ፤ ከከባድ ድካም እና ከማያቋርጥ ቁፋሮ በኋላ ሃዋርድ የለያቸው ቦታዎች ሁሉ አሁንም የተሳሳቱ ሆኑ። የዚህን ጊዜ ባለጸጋው ፋይናንሰር እንዲህ በማለት ጮኸ፦ 'ሃዋርድ ሆይ፡ ከዚህ እንሂድ እንሂድ፡ ይህን ሸለቆ እንልቀቅ፡ በእውነት ጊዜዬንና ገንዘቤን አባከንከብኝ' አለ።

ሠራተኞቹ ቦታውን ለቀው ለመሄድ በሚዘጋጁበት ወቅት፣ ሃዋርድ በፍጥነት የሸለቆውን ካርታ ወስዶ እንደገና ማየት ይጀምራል፡ ቦታው እዚህ መሆን አለበት፡ የመጨረሻ ስሌቴን አደርጋለሁ፡ ተስፋ በፍፁም አልቆርጥም በማለት፡ ሃዋርድ በፍጥነት ቦታውን በሥዕል በመለየት ለሠራተኞቹ ይገልጻል። ሃዋርድ ቁፋሮው የሚካሄድበትን ቦታ በማመልከት ሠራተኞቹ እንዲቆፍሩ ሲያዛቸው፣ ፋይናንሰሩ ሰምቶ፡ "ሃዋርድ አቁም" ይህ ሁሉ ሙከራ ተደርጎ ምንም ስላልተሳካ፡ ተጨማሪ ጉልበት እና ገንዘብ ከማባከናችን በፊት ከዚህ ቦታ እንሂድ በማለት በድጋሚ ሃዋርድ ላይ ጮኸበት። እለቃ አንድ የመጨረሻ ዕድል ስጠኝ፣ አንድ ዕድል፡ በማለት ይለምነዋል። እሺ የመጨረሻ አንድ ዕድል ሰጠሁህ አለው።

ከዚያም ሃዋርድ እንዲህ አለ፣ በዚህ ምትሃታዊ ኹነት ነበር እልህ አስጨራሽ ጥረት በማካሄድ ወደ መሬት ገብተን ገደብ የለሽ ህልማችንን ማሳካት የቻልነው፣ እጅግ የላቀ የሆነ ግኝትም አገኘን .. "የቱታንካሙን ውድ ሀብት"!።

<u>**መልዕክት 50፡**</u> ሃዋርድ ታዲያ ከዚህ ሁሉ አቋሙ በኋላ ለተስፋ መቁረጥ እጅ ባለመስጠቱ ሀብቱ አይገባውምን?

ጅራፍ ያላቆመው ቁርጠኝነት

ኢማሙ አሕመድ ኢብኑ ሐንበል ባንድ ወቅት የደረሰባቸውን መከራ ሲገልጹ እንዲህ ብለው ነበር፦ አለንጋዎቹን ሲያመጡ አል-ሙዕተሲም ወደ እነርሱ ተመልከቶ ገራፊዎቹን ኑ ወደዚህ በማለት አዘዛቸው፣ አንዱ ወደ እኔ መጣና ሁለት ጊዜ መታኝ። አሁንም በተመሳሳይ ሁኔታ በአለንጋው ለ19 ጊዜ ስመታ እሱም አጠገቤ ቆሞ፦ አሕመድ ለምን ራስህን ታጠፋለህ?! በአላህ ይሁንብኝ እኔ ላንተ አዛኝ ነኝ እነዚህን ሰዎች ልታሸንፋቸው ትፈልጋለህ? ይላል። ከነሱም መካከል አንዳንዶቹ፦ ወዮልህ መሪያችን ፊትለፊትህ ቆሟል ማለት ጀመሩ። ከፊሎቹም፦ የሙእሚን አዛዥ ሆይ ደሙ በእኔ ላይ ነው ግደለው ያሉም ነበሩ። አል-ሙዕተሲም የዚህን ጊዜ እየሳቀ አሕመድ ሆይ አሁንስ ምን ትላለህ? አላቸው፣ ኢማሙ አሕመድንም፦ "ከአላህ ኪታብ (ቁርዓን) ወይም የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ሱና ውስጥ "ቁርዓን ፍጡር አይደለም፣ የአላህ ቃል ነው" የሚል አንድ ማስረጃ ስጠኝ፣ እኔም ለመመስከር እንዲመቸኝ ይላቸዋል!

አል-ሙዕተሲም ተመልሶ ተቀመጠና ገራፊዎቹን ወደ ፊት በመጥራት፡ አሕመድን እጅህን ነው የምቆርጥልህ እያለህ ነው እንዲሏቸው ይነግራቸዋል። ከዚያም አል-ሙዕተሲም በድጋሚ ተነሳና፡ ኸረ አሕመድ ተው መልስልኝ አላቸው። ሰዎቹም ወደ እኔ በመቅረብ አሕመድ ሆይ መሪህ ፊትለፊትህ ቆሟል እኮ መልስለት እንጂ ማለት ጀመሩ፣ እጆቻችንም እንዲራሩ አሏቸው። የሙእሚን አዛዥ ሆይ ከአላህ መጽሐፍ (ቁርዓን) የሆነ ማስረጃ ስጠኝ እና እኔም ለማመን እንዲመቸኝ አሉት። ከዚያም ተመልሶ ገራፊዎቹን በመጥራት አዘዛቸው፤ ከዚያም ገራፊው ወደኔ ቀርቦ ሁለት ጊዜ መታኝና ዘወር አለ። ኢማሙ አሕመድ የግርፋቱን ሁኔታ ሲናገሩ እንዲህ አሉ፦ ከድብደባው ከብደት የተነሳ አዕምሮዬን ሁሉ ስቼ ነበር።

ከአስከፊው ድብደባ እና እስራት በኋላ አል-ሙዕተሲም ኢማሙ አሕመድ ይሞታሉ፣ ሕዝቡም ያምጽብኛል ብሎ በመሥጋት ድብደባውን አቁሞ ለቤተሰቦቻቸው አስረከበ። ኢማሙ አሕመድ ኢብኑ ሐንበል ረጃጅም ተራራዎች

ሊሸከሙት ያልቻሉትን ችግር እና መከራ እንዲታገሱ ያደረጋቸው ምን ይሆን? ከጽናቱ እና ከቁርጠኝነቱ ወደ ኋላ እንዳይመለሱ ያደረጋቸውስ ምን ይሆን? ምንም እንኳን አደገኛ ጠላት አጥብቆ ቢደዛቸውም እና እንደማያመልጡ ቢረዱም ከነፍሳቸው ውስጥ ተስፋ መቁረጥን ያባረሩትስ ለምን ይሆን?

> <u>መልዕክት 51፡</u> ነገሩማ በአላህ ላይ ያደረጉት ተስፋ ሲሆን፡ በቀላሉ በጌታቸው ላይ ተስፋ የማይቆርጡ በመሆናቸው ነበር። በዚህም ነው አማኞች ከመለኮታዊው ብርሃን ኃይላቸውን የሚያገኙት፣ በዙሪያቸው ያለው ሁኔታም መመራትን ሲለግሳቸው የሚቀበሉት። አላህ ኢማሙ አሕመድን ሰፊውን ምሕረት ይማራቸው።

◆◆◆◯◆◆◆

በፈጣሪህ ላይ መልካምን ጠርጥር

አላህን በመልካም መጠርጠር ታላቅ ልባዊ አምልኮ ሲሆን፣ ያለዚህ መልካም ጥርጣሬ የባሪያው እምነት ሙሉ አይሆንም። ምክንያቱም ይህ ተግባር የተውሒድ እምብርት እና ግዴታ የተደረገ ነገር ነው። በአላህ ላይ መልካም ጥርጣሬ ማለት ለልዑሉ አላህ የሚገባውን እምነት መስጠት ማለት ነው። ለክብሩ የሚገባውን ማመን እና በተዋቡ ስሞቹ እና ታላላቅ ባህሪያቱ የሚፈለግበትን እምነት መስጠት ማለት ነው። የአማኝ ሕይወት የሚለካው ሁሉን ቻይ የሆነውን አላህን በሚያስደስት መልኩ በእርሱ ላይ መልካምን በመጠርጠር ነው፡ የአላህ ባሪያ ማለት ፈጣሪው መሃሪ መሆኑን፣ ከጭንቀቱ የሚገላግለው እና ሐዘኑን የሚያስወግድለት መሆኑን የሚያምን ማለት ነው። በዚህም ምክንያት አላህን በማላቅ፣ መሃሪ መሆኑን የሚገልጹ እና በብቸኝነት ለሚያመልኩት ቃል የገባበትን በማውሳት የተወረዱ አንቀጾችን እና ሃዲሶችን ለማሰላሰል ይጠቅመዋል።

አላህ (ሱ.ወ) "እኔ ባሪያዬ በጠረጠረኝ ቦታ አገኛለሁ" ይላል። ይህን አባባል ካብራሩት መካከል